# ኢትዮጵያ አገራችንን
# ከጥፋት ለማዳን በጋራ እንታገል

አበበ ዋሲሁን

አገራችን ኢትዮጵያ በጣም አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። በአሁኑ ፍጥነትና ጥልቀት ችግሮች ከተደራረቡና ከተወሳሰቡ ውሉ በጭራሽ ይጠፋና፤ እንደው የስይጣን ጆሮ አይሰማና፤ አሁን የምናውቃት ኢትዮጵያ እንደ አገር መቀጠሏ አጠራጣሪ/አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። ወያኔ ብዙ ወጥመድ እየዘረጋልን ነው። የጎሳው ፖለቲካ አልበቃ/አልሳካ ብሎት፤ አሁን ደግሞ በሃይማኖት ለማበጣበጥ እየሞከረ ነው። በእስልምና በኦርቶዶስ ተከታይ ኢትዮጵያን መካከል የማያስፈልግ ብጥብጥ ለማስነሳት እየተወራጨ ነው። ከዚህ አጣብቂኝ መስቀለኛ መንገድ በአቸናፊነት ለመውጣት የተቃዋሚ ድርጅቶች በአስቸክይ ሁሉን አቅፍ ጉባዔ ማለት የፖለቲካ ድርጅቶችን፡ የሲቪክ ማህበራትን፡ የሃይማኖት አባቶችን፡ የአገር ሽማግሌዎችን፡ ምሁራን እንዲሁም ወጣትና ሴቶች ማህበራትን ወዘተ ተሰብስበው የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በጋራ መርምረው፤ ምን መደረግ አለበት/ምን ይሻላል፤ በሚለው ጥያቄ ላይ መክረው ዘክረው በአጣዳፊ ምላሽ መስጠት አማራጭ የሌለው የአገር ሀላፊነትና ከባድ አደራ ነው።

የሲቪክ ማህበራት ማለት የመምህራንና የነጻ ጋዜጠኞች አሁን በራሳቸው አነሳሽነት የጠሩትን ሁሉን አቀፍ ጉባዔ እድል ሊስጠው በበጎ ዓይን ሊታይ ይገባል ። እስከአሁን ድረስ ህብረቱ ማለት ኢዴሃህ ለጥሪው አወንታዊ መልስ ስጥቷል ሌሎችም እየተጠበቁ ናቸው። የጉባዔው ተሳታፊዎች በብድን፡ በድርጅት፡ በግለስብ ይሁን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሳባቸውን አቅርበው በመደራደር ኢትዮጵያ አገራችንን ለማዳንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዴት እንመስርት በሚለው ላይ ትኩረት በመስጠት የጋራ አጀንዳ ቀርጸው፡ ትግሉን ማፋፋም አለባቸው። ሁሉም ተሳታፊዎች አጉል የማያስፈልግ ንትርክ፤ ብልጣብልጥነትንና ጮሌነት እርግፍ አድርገው በመተው፡ እንዲሁም ለርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ሳይታለሉ፡ በቀና መንፈስና አርቆ አሳቢነት ችግሮችን መርምረው ሁሉን የሚያስማማ አንድ መርሃ ግብር ቀይስው

በተግባር ለመተርጎም ቁርጠኛ ውሴኔ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተሳታፊዎች ይህን የተባለውን ማድረግ ከቻሉ በርግጥ የጉባዔ አላማ ግቡን መታ ማለት ነው። በዚህም የተቃዋሚ ጎራ ሲጠናከር፡ በአንጻሩ ወያኔ አቅመቢስ/ደካማ ይሆናል ማለት ነው። የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲውም ማለት የጎሳም ይሁን የሃይማኖት ሁሉም ተራ በተራ እንዲከሽፍ ይረዳል ማለት ነው። ይህ ለሕዝባችን ትልቅ ደስታን የሚሰጥና እንዲሁም ሞራሉንና ወኔውን ይበልጥ የሚያጠናክርና ለበለጠ ትግል የሚያንቀሳቅሰው ይሆናል። የግንባሩም ሁሉን ያቀፈ በመሆኑ ትግሉን በአስተማማኝ ይመራል፡ የተቃዋሚ መሪዎችም መምሪያና አቅጣጫ በመስጠት ታግለው ያታግላሉ ማለት ነው። ሕዝባችንም እንዳለፈው ጊዜ የመሪ ያለህ ብሎ አይጮህም፤ አያማርርም። ሕዝባችንም በጋራ ግንባሩም ላይ ሙሉ እምነት ያድርበታል፡፡ የግንባሩ አባል ድርጅቶችን ሲያጠፉ ይመክራል፤ ይገስፃል፤ መልካም ሲሰሩ ያበረታታል። ሕዝባችንም በሁሉም መስክ ማለት በገንዘብ፡ በቁሳቁስ፡ በጉልበት፡ በእውቀቱ፡ በህይወቱ ትግሉ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመክፈል ዝግጁነቱን ያረጋግጣል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነት ትግል ማድረግ ስንችል ብቻ ነው በአቸናፊነት የአገራችን ህልውና ለማስጠበቅ፤ ሰላምና እርቅ፤ የዴሞክራሲያዊነት ሥርዓት፤ ልማት ማምጣት የምንችለው።

በአለፈው አስራ አምስት አመታት የተቃዋሚው ጎራ ብዙ ችግሮች ገጥመውታል፤ ድክመቶችም ታይተዋል፡ አንዳንዶቹም በጊዜው ሳይታረሙ እስከ አሁን እንድቀጠሉ በመደረጉ ወያኔ እንደፈለገ ያሻውን በማድረግ ላይ ይገኛል። የወያኔ የግፍ አገዛዝ፤ ስብዓዊ መብት ረገጣው፤ ግድያው፡ እስራቱ የምታውቁትና መደጋገሙ አስልቺ በመሆኑ ወደ የራሳችን (ተቃዋሚው ጎራ) ድክመቶችና የመላምት መፍትሂ አሳቦች ላይ ማተኮሩ መልካምና ጠቃሚ መሆኑ በአሁን ባለንበት ወቅት አጠያያቂ ሊሆን አይችልም።

ይህን በማጤን አሁን የታሰበውን የሁሉንም ተቃዋሚዎች ጎራ ያቀፍ ጉባዔ ማንም ይጥራው ማን ቁምነገሩ ለጥሪው ክብደት ሰጥቶት ስብሰባው እንዲደረግና ስኬታማ ሆኖ የጋራ የትግል ግንባር መፍጠሩ ላይ ነው። በዚህ የጉባዔ ሂደት ውስጥ አንድ ትኩረት ሊስጠው የሚገባ ትልቅ ጉዳይ “አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” እንዳይሆን የነበሩና ያሉ ችግሮችና ድክመቶች በገንቢነት መልኩ አጽንኦት ተሰጥቶት ውይይት እንዲደረግበት በማስብ ወሳኝነት አለው። እንዴት አሁን ያለንበት የቀውስ ደረጃ ልንደርስ ቻልን? ተቃዋሚዎች በጋራ

አብረው እንዳይሰሩ ያገዳቸው ችግሮችን እንዴት እንፍታቸውና የጋራ ትግል ግንባር እንመስረት? አዳዲሶቹን የተቃዋሚ ድርጅቶችና ደጋፌዎቻቸው የተናጠል ትግል ብዙ መሰዋእዕትነት ከመጠየቁ ባሻገር የትግል ዘመኑ የሚያራዝመው መሆኑንን ካለፈው የትግል ማህድር ለመረዳት/ለመማር ለምንና እንዴት አልሞከሩም? ለመጭው ትግል የተቃዋሚ ጎራ በሙሉ ከእግዲህ ወዲህ በምንም ዓይነት መንገድ ለወያኔ ተራ በተራ በተናጠል ለመምታት ምቹ ሆኖ መቅረብ መቆም አለበት።

በአለፉት አስራ አምስት ዓመታት የጋራ የትግል ግንባር ለመፍጠር ብዙ ሙከራዎች ማለት በኢድህቅ፡ ኢታፖድ፡ ህብረት፡ ቅንጅት፡ በቅርቡ ትብብር ሙከራ ተደርጓል፡፡ ምንም አልተስራም ለማለት ሳይሆን የታሰላቸውን ግብ አልመቱም ለማለት ነው። አሁን ሊመሰረት ለታሰበው ጠንካራ የጋራ ግንባር ከአለፉት የትግል ተመክሮዎች ምን አዎንታዊና አሉታዊ ትምህርት/ተመክሮ ሊቀስም ይገባል? አንዳንድ የብሄር ብሄረስብ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትንና የአገር ልዑላዊነትና እንደራሳቸው አድርገው ለመውሰድ እንቸገራለን ለሚሉ፤ እንደቀረው ዓለም የብዙ ብሄር ብሄረስብ የሚገኙበት አገሮች አንድነት በልዩነት የሚለውን ፅንስ አሳብን ተቀብለው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በኩልነት በመከባበር ሲኖሩ ይታያል። ስለዚህ ለሚያንገራግሩ ድርጅቶች በጉባዔ እንዲሳተፉ ምን መደረግ አለበት? በእነዚህ ድርጅቶች ላይ ሕዝባችን ምን ዓይነት ግፊት/ጫና ሊደረግባቸው ይገባል/ይችላል? የተቃዋሚ ጎራ ሊገነዘብ የሚገባ ወያኔን ከሥልጣን አውርዶ በምትኩ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት አጥብቅ ከመታገል የበለጠ ምንም ቅዱስ ተግባር አለመኖሩን ነው። የግንቦቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ ለአንዴም ለሁሌም አለመፈለጉን ነው። በግንቦቱ ምርጫ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎን ማወቅ እንዲሁም በትግሉ ውስጥ በግለሰብና በድርጅት የተከሰቱና የታዩ ቆራጥነት፡ ክህደትና አድርባይነት እንዲሁም ስርጎ ገቦች ያስከተሉት እንድምታ ምንድን ናቸው?

የአጭር ጊዜ ተግባር በመመሪይ ደረጃ ሕዝብ የመረጣቸው መሪዎቻችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለማስፈታትና የሕዝብ ድምፅ ይከበር የሚለው ትኩረት ሊስጠው ይገባል። ሌላው እንዳለፈው ጊዜ በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ጉንጭ አልፋ ንትርክ መተው ለምሳሌ የትግል ስልት መረጣ ውስጥ ተገብቶ ስላማዊ ትግል ወይስ አመጽ ይሻላል ብሎ በአጉል ጭቅጭቅ ጊዜን ማባከን መተው ያለበት ጉዳይ ነው። ሁሉንም ነገር የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚወስንው፡ ስለሆነ በሁሉም መስክ

መዘጋጀቱ ጠቃሚ ነው። አንዱ ላይ ብቻ ሙዝዝ ማለቱ እንደው "ካልኩ/ካጠፋሁ አይመልስኝ" አባባል ትግሉን ይጎዳል፡ ወያኔንም ይጠቅማል።

የአገራችን እናድን ጥሪ ድንገት እንደው እንደውሃ ሙላት የመጣ ጉዳይ አይደለም። ከግንቦት 7 ምርጫ በኋላ ኢድሃህ በሁለተኛው ልዩ ስብሰባው ጊዜ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ መርምሮ ትግሉን በህብረት ለማቀናጀት እነሆ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ጥሪ ካቀረበ አንድ ዓመት ሆኖታል። አሁን በአዲስ መንፈስ የሲቪክ ማህበራት ማቅረባቸው ትክክለኛ ናቸው። ስለሆነም ጥሪው በበጎ ዓይን ታይቶ አወንታዊ ምላሽ ሊስጠው የሚገባ ነው። የዚህ ጉባዔ መሳካት ተጠቃሚ የሚሆነው ሁሉም ነው ማለት አገራችን ከገባችበት አዘቅት አውጥተን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከመስረትን ሁሉም ችግሮች በቅደም ተከተልና በየመልኩ ይስተናገዳል አባባሌን ግልጽ ለማድረግ ችግሮች ይፈታሉ ማለት ነው። ከዚያ ድርጅቶች በነጻ ፕሮግራማቸውን አቅርበው በሥነስርዓቱ ይወዳደራሉ ማለት የዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት በሚፈቅደው መስረት ለተወስነ ጊዜ ሕዝባችን የተመረጠው ፓርቲ ያገለግላል ማለት ነው።

## አጠቃላይ ግንዛቤዎችና ጥቆማዎች

1. የዛሬ አስራ አምስት ዓመት ወያኔ የሽግግር መንግሥት መስረትሁ ባለበት ጊዜ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑትንና ሁለት ሥርዓቶች የታገሉ የኢድሃቅ አባል ድርጅቶች ማለት ኢህአፓና መዔሶን እንዳይካፈሉ ተከለከሉ ይባስም ተብሎ ኢሕአፓ ፀረ-ስላም ተብለው ተፈረጀ። የአሁን ተቃዋሚዎች የወያኔን ባህሪ ጠንቅቀው ባለማወቅ እስቲ ለወያኔ ጊዜ እንስጠው ያሉም አልጠፉም። ለምሳሌ በኢሕአፓና በወያኔ መካከል የግል ጠብ እንዳለ አድርገው ለማቅረብ የዳዳቸውም አልጠፉም። ጠቡ የመተከል ጉዳይ ማለት የራዕይ ነው፡፡ ወያኔና ተለጣፊዎቹ የሚያምኑት በመጀመሪያ የብሄር ብሄረስብ ችግር መፈታት አለበት ማለትም "የራስን እድል በእራስ መወስንና እስከመገንጠል" የሚለው የስታሊን ንድፈ አሳብ መከበርና በሥራ መዋል አለበት፡ ከዚያ በፍላጎታቸው ከፈለጉ ኢትዮጵያዊ መሆን ይችላሉ እነወይኔ ሲሉ የኢሕአፓ አቅዋም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ እንደራደርም፡ እንዲሁም የቅኝ ግዛት የሚባለውን

ጥያቄ/ጉዳይ አልቀበልም ፅንስ አሳብም ለኢትዮጵያ አይሰራም ማለቱ ነው። ይህን ዓለም ያውቀውን ሀቅ አጣመው ለማቅረብ የሚሞክሩ አጉል ልፋት ነው፡፡ ኢሕአፓ እንደህብረት (ኢዴሀህ) አባላት ሁሉ የሚለው ለኢትዮጵያ በመጀመሪያ የሚያስፈልገው አንድነቷ ተጠበቀ  የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ ማምጣት ነው።  ዛሬ ሕዝባችን ስለሁሉም ድርጅቶች እንዲሁም አንዱ ድርጅት ስለሌላው ድርጅት ጠንቅቆ ያውቃል፤ ስለዚህ መሸዋወድ አይቻልም። ኢሕአፓ የዴሞክራሲና የገበያ ሥርዓትን የተቀበለው ገና ደርግ በስልጣን ላይ እያለ፡ የሶቪየት ህብረትና ታሪካዊው የጀርመን ግንብ ሳይፈርስ ነው። አባባሌ ለመኩራራት ሳይሆን ሀቁ እውነቱን ለሁሉም ለማሳወቅ ነው። ሌሎች ድርጅቶች ከደርግ በኋላ የተመሰርቱ ሁሉም የዴሞክራሲያ ሥርዓት መመኘታቸው እስዬው የሚያስብል ነው።

2. ተባብረን አገራችን ከጥፋት ለማዳን የሚያግደን ምን ሀይል መኖር የለበትም። የቀይ ሽብር ተበዳይም በዳይም ለመውቃቀስ ምናልባትም ይቅር እግዚአብሔር መባባል የሚቻለው የሁላችንም የሆነችውን ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን ስንችል ነው። አለማስተዋላችንና አለመቻላችን ይሳዝንል። አሁንም ጊዜው ስይመሽብን አገር ማዳኑ ላይ መረባረብ ብልጥነትና አዋቂነት ነው። በህብረት ለመታገል ፍላጎት ማሳየት ድክመት አይደለም። አዳዲስ ድርጅቶችና ወደፊት የሚቋቋሙ ድርጅቶች የረጅም ጊዜ የትግል ተመክሮ ካላቸው ድርጅቶች መማርና መማማሩ አዋቂነት ነው ስህተቶች እንዳይደገሙ ይረዳል። ለምሳሌ ስለወያኔ ማንነት ከማንም በተሻለ ኢሕአፓ ጠንቅቆ ያውቃል። እስቲ ከወያኔ ትምህርት እንውሰድ የዓላማ ግብ ለመፈጸም ምንም ከማድረግ አይመለስም። ከሻቢይ በተጣላ ጊዜ ያ አልወደውም ያለውን ስንደቅ ዓላማችን ለጥቅሙ ሲል አንግቦ “እሪ አገር ተወረረ” የድረሱልኝ ጥሪ፡ አደረገ። በዚያም ሳቢያ 70ሺ ያላነ ሕዝባችን ውድ ሕይወቱን ገበረ። አሁን ደግሞ ዓለም በሙሉ ያወቀውን ገንጣይ አስገጣይ መሆኑ ደብቆ፡ በሱማሊያ በኩል ዳር ድንበር አስረክባለሁ በማለት ድንባሩ ጥፍቶበት ኪስማዩ ደርሶአል። ታዲያስ ይህን ምን ልንለው እንችላለን? ዳርድንብር ማስከበር? ይህ አድራጎት ያካባቢው አገሮች “እንኳን ዘንቦብሽ…” ዓይነት በአገራችን ላይ የዐረቡ ዓለምና ጎረቤቶቻችን ጥርሳቸውን እንዲነክሱብን አያደርግም?

3. ኢ.ድህቅ የብሄራዊ እርቅና ስላም ጥሪ ለወያኔ በማቅረብ በጎፈቃድ አሳይቶ ነበር፡ በአንጻሩ ወያኔ ጥሪውን ያየው እንደድክመት ነበር። ይባስ ብሎም የስላም መልክተኛውን አቶ አበራ የማነአብን በተልካሽ ክስ የሃያ አምስት አመት ፍርድ ተበይኖበት በእስር ላይ ይገኛል፡፡ አረ ስንቱ ተውርቶ ያልቃል እንድው የጉዱ ጉድ የወያኔ ተግባር። በ1991 ዓ. ም. ወደ አዲስ አበባ ለመድረስ በሚገስግስብት ጊዜ የኢ.ሕአፓ አመራር አባላት ማለት እንደ ደብተራው ፀጋዬ ገብረ መድህን መተኪያ የሌላቸውንና ሌሎች የኢ.ሕአፓ አባላትን ይዞ እስካሁን ይሙቱ ይኑሩ ደብዛቸውን አጥፍቶ ነው ያለው። ከዚህ የምንማረው ለመጭው ትግል ዘመን ወያኔ የሚለፈልፈውን/የሚወሽከተውን ማድመጥ ሳይሆን በተግባር የሚያደርገውን መገንዘብ/ማየት ጠቃሚ ይሆናል።

4. የተቃዋሚ ድርጅቶች ድክመት በአንድ ላይ ለመቆም አለመቻል ለወያኔ ጥንካሬ እንደስጠው፤ አንዱ ድርጅት ወይም ክልል ለምሳሌ ወያኔ ሥልጣን በያዘ ስሞን በአማራው ሕዝብ ላይ ያ ሁሉ በደል ሲፈጸም ሌላው ዝም ብሎ በማየቱ፤ በየተራ ሁሉም በደብብ ሕዝብ፡ በኦሮሞ ሕዝብ፡ በአኝዋክ ሕዝብ፡ በኢትዮጵያ ሱማሌ ሕዝብ ወዘተ የደረስው ግፍና በደል የዓለም አቀፍ የስብአዊ መብት ተምጋች ድርጅቶች የመዘገብት ነው። በአንዱ ላይ የሆነው በሌላው እንደሆነ ወስደን እምቢ አሻፈረኝ ማለት መቻል አለብን።

እንግዲህ እንደአቅሜ ገንቢ ናቸው ብዬ ያስብኩትን የመንደርደያና መፍትሔሄ አሳቦችን ስንዝሪያለው። አማራጭ አሳብ/አስተያየት ከተቃዋሚ ጎራ እንዲያቀርብ እጋብዛለሁ፤ ለመታረምና ትችት ለማስተናገድ ዝግጁ ነኝ። የቀረብት ጥያቄዎችና መላምት አሳቦች ለውይይት እንዲያመች ታስቦ ነው፡ ማንንም ለመውቀስ ለመክስስ አይደለም። ዋና አላማው ስህተቶች/ድክመቶች እንደገና እንዳይደገሙ ለመጠቆም ነው።ልዩነት ለአንድነት እስከሆነ ድረስ ጤናማና ጠቃሚ ከመሆኑ በላይ የአሳብ መቀራረብንና ጥራት እንዲሁ የመንፍስ ጥንካሬን ያስገኛል። ሆኖም አንዳንድ የብሄር ብሄረስብ ድርጅቶች ኢ.ትዮጵያዊነት እንደ መደራደሪያ ነጥብ/ጥያቄ አድርው ሲያቀርቡት ይስተዋላል፤ ይህ ሁላችንንም ይጎዳል። ይህ አድራጎት የህዝባችንን አብሮ የመኖር ፍላጎትና መብት ከመጻረሩ በላይ፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዐት ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ትግል ላይ አሉታዊ አንደምታ ይፈጥራል።

እዚህ ላይ አንድ አሌ የማይባል ቁምነገር በአገራችን ለረጅም ጊዜ የብሄር ብሄራስብ ጭቆና ነበር አሁንም አለ። መፍትሄው ግን መገንጠል አይደለም። በእኔ አስተሳስብ ችግሩ ሊፈታ የሚችለው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ነው። በአስራ አምስት ዓመት ተመክሮአችን የወያኔ መፍትሔ በመጀመሪያ የብሄር ብሄረስብ ችግር ፈተን በኋላ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንሂድ ያለው እንዳልስራ እያየነው ነው። በተቃራኒው የብሄርስቦች እኩልነታቸው፡ ስባዓዊ መብታቸው ጥቅማቸው ሳይረጋገጥ/ስይከበር፡ ወይኔ ያን ሁሉ ለፍፎ በተቃራኒው ወደ ፍጹም አንባገነንነትና አሸባሪነት ተቀይሮ በአገርም ውስጥ በውጭ አገር ማለት በጎረቤት አገሮች ለምሳሌ ሱማሌ ውስጥ በወራሪነት ገብቶ እያተራመስ ይገኛል። ስለዚህ ወያኔን ከሥልጣን አስወግዶ ዘላቂና ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ሁሉም በኩልነትና በመከባበር የሚኖርባት አገር መገንባት የሁላችንም አላፊነት ነው። ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳን።